www.ethiopianorthodox.org

# «መልካም እረኛ እኔ ነኝ» ዮሐ.፲፥፩–፲፩

ከመምህር ቀጸላ መንግሥቱ



ይህን ቃል የተናገረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን በመልካም እረኛ የተመሰለ እርሱ በአባግዕ የተመሰሉ ምእመናን ናቸው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱን በመልካም እረኛ መስሎ የተናገረበት፣

፩. በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ ፱ እንደተጻፈ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው በደረቅ ግንባር ዓይን ፈጥሮ ያዳነውን እንዳ ያመሰግንና እንዳያምን ባንገላቱት ጊዜና እርሱንም የጸረፉበትን ኃይለ ቃል ለማስተካከል ነው።

ሀ. ሑር ሀብ ስብሐተ ለእግዚ አብሔር ንሕነሰ ነአምር ከመ ኃጥእ ውእቱ ዝ ብእሲ፤ ያዳነህ እግዚአ ብሔር ነው እንጂ ይህ ሰው ኃጢአተኛ በመሆኑ አላዳነህምና ለእግዚአብሔር ምስጋና አቅርብ ብለውታልና ኃጥእ እንዳልሆነ ኄር ኖላዊ መሆኑን በሥራው ለመግለጥ፤

ለ. እግዚአብሔር ሙሴን ቃል በቃል እንደ ተነጋገረው እናውቃለንና የሙሴ ደቀ መዛሙርት ነን በማለት ከፈጣሪያቸው ፍጡርን ከመምረ ጣቸውም በላይ «ወለዝንቱሰ ብእሲ ኢነአምሮ እም አይቴ ውእቱ» ይህን ሰው ግን ከየት እንደመጣ አናውቀ ውም ስላሉት ከየት እንደመጣ ለማስ ረዳት ነው። ይህም ቃል፣ ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ ብሎ ወደ ፈጣሪያቸው ሕዝቦች እንዲሁም ወልድየ ዘበኩርየ ብሎ ወደ መረጣ ቸው ወገኖቹ መጣ። እነሱ ግን አልተ ቀበሉትም ተብሎአልና። ውስተ ዚአሁ መጽአ ወእሊአሁሰ ኢተወክ ፍዎ እንዲል፤

ሐ. «አንሰ መጻእኩ ለኰነኔ ዝንቱ ዓለም ከመ እለ ኢይሬ እዩ ይርአዩ ወእለ ይሬእዩ ይዑሩ» አናውቅም በሚሉ ሐዋርያት ልፈርድላቸው፥ እናውቃለን በሚሉ ፈሪሳውያን ልፈርድባቸው መጥቼአለሁ ብሎ ነበርና ለምሕረት እንደ መጣ ለማጠየቅ ነው።

፪. «አማን አማን እብለክሙ ዘኢቦአ እንተ አንቀጽ ውስተ አጸደ አባግዕ ወአርገ እንተ ካልዕ ገጽ ሠራቂ ወጕህልያ ውእቱ» ያላቸውን በግብ ሐዋርያት ምዕ.፫.... የተወቀሱትን ቴዎዳስ ዘግብጽና ይሁዳ ዘገሊላ የመሰሉ ናቸው። ቴዎዳስ ዘግብጽ እኔ አምላክ ነኝ በማለት አራት መቶ ያህል ሰዎችን አስከትሎ ነበር፤ ነገር ግን ይህ መሰሐቲ ጠፋ፣ አምነው የተከተ ሉትም ሁሉ ጠፉ፣ እንደ ምናምንቴም ሆኑ ይላል። ይሁዳ ዘገሊላም በዚያው ወራት ብዙ ሰዎችን ከእውነተኛው እምነት አስፈንግጦ አስኮብልሎ በማሸፈት እርሱን እንዲከተሉና እንዲያምኑ ስላደረገ እርሱም ጠፋ። ያመኑበትም ሁሉ ጠፉ፤ ተቀሰፉ። ምክንያቱም ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባና የማይወጣ ሌባና ወንበዴ ነው ተብሎ ተጽፎአልና።

ደግሞ ሌባ ሊሰርቅ፣ ሊያርድና ሊያጠፋ እንጂ ለሌላ አይመጣምና ነው። በአንጻሩ ግን መልካም እረኛ ሰውነቱን ለበጎች አሳልፎ ይሰጣል። እኔም ሕይወት እንዲሆንላቸውና እንዲበዛላቸው ስለመጣሁ መልካም እረኛ እኔ ነኝ አለ።

፫. በብሉይ ኪዳን የነበሩትን መኳንንት፣ መሳፍንት በሕዝቅኤል አድሮ ሲገስጻቸው «አሌ ሎሙ ለኖሎተ እስራኤል ወኢርእዩ አባግዕየ እለ ኮኑ ኖሎተ ርእሶሙ» ብሎአ ቸዋል። ሕዝ.፴፬፥፩–፲፰፤ ኢሳ. ፵፥፲፩።

እኒህ የእስራኤል መሪዎች ጠባቂዎች መሳፍንቱና መኳንንቱ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ሥል ጣን ራሳቸውን በድሎት፣ በምቾት፣ በተድላ በደስታ ጠበቁበት፣ እንዲ ሁም ከሥጋዊ ጠላት ከረሃብ፣ ከንዴት በመጠበቅ ተገለገሉበት እንጂ ራሳቸውን ከክሕደት፣ ከኃጢአት አልጠበቁበትም ምክንያቱም መሾማ ቸው መሳፍንቱ፤ መኳንንቱ ህዝቡን ሊጠብቁ ከዓመፅ ሊርቁ፣ ለተራበ በግብር ለተበደለ በነገር ሊገኙ ነበር። እነርሱ ግን «በልዑ ሰብሐ» ሰብህ ትርፍ ሥጋ ነው። ስለዚህ «ኢትንሣእ ኀልያነ» የምትል ሕግ እያለቻቸው ትርፍ ገንዘብ ይበላሉ፤ መማለጃ ይቀበላሉ። ይህ ተግሣጽ ለመኳንንቱ ብቻ አይደለም፤ የሹመት ማዕረግ ላላቸው ሁሉ ለሚዳኙ ነው እንጂ ዘጸአ ፳፫፥፰። «ወይለብሱ ጸምረ» ከድሆች ወስደው በተረፈ ልብሳ ቸውን ይገፋሉ የላም መንጃ፣ የሸማ መከንጃ፣ የማር መቅጃ፣ የሠፋሪ፣ የቆጣሪ የሚሉት አለና። «ወዘደከመ ኢያጸንዑ» እንደ ተባለው በጣዖት የደከመውን በአሪት አያጸኑትም። እንደ ኢዮሳፍና፣ ኢዮሳፍጥ «ሑሩ ወመሐሩ ኦሪተ ውስተ ኩሉ ምድረ ይሁዳ» ብሎ ባወጀ ጊዜ በመላው በምድረ ይሁዳ ኦሪት ተሰብካ ነበር። እነርሱ ግን በአምልኮተ እግዚአ ብሔር፣ በገቢረ ጽድቅ ሕዝቡን መምራት ሲገባቸው ለሥጋዊ ፍላጐ ታቸውና ለምድራዊ ተድላ ማመ ቻቺያ አደረጉት «ወዘሐመ ኢትፌ ውሱ፣ ወዘተሰብረ ኢትሔድሱ» እንደ ተባለው በክሕደት



2nd year, Number2, Meskerem 1992

www.ethiopianorthodox.org

የታመመውን በሃየማኖት አይፈውሱትም፤ በኃጢአት የተሰበረውን በንስሐ አይጠግኑትም «ወዘኀየ ኢይመይጡ» ግብር መሮት አገዛዝ ጸንቶበት በስደት አገር ጥሎ ቁርበት ጠቅልሎ የሄደውን ባዋጅ ከርስቱ ከነገዱ አይመልሱትም። «ወዘተገድፈ አይሐስሱ በውዋዩ» የጠፋውን በማጣት አይመልሱትም። እውነተኛው እረኛ ግን ከነዚህ የተለየ በመሆኑ «ለልየ እርዕዮሙ ለአባግዕየ ወአነ አዐርፈክሙ ይቤ አዶናይ እግዚአብሔር» እኔ በካህናት አድሬ እጠብቃችኋለሁ፤ ለነገሥታት ከመገዛት አሳርፋችኋለሁ ለጊዜው ይህ ሲሆን ፍጻሜው ግን ሰው ሁኜ ሥጋ ለብሼ አድናችኋለሁ ማለትን ያሳያል። «ንዑ ኀቤዩ ኩልክሙ ሥሩኃን ወክቡዳነ ጾር ወአነ አዓርፈክሙ» ማቴ.፲፩፥፳፰ ሸክማችሁ የከበዳችሁ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ «እስመ አርዑት የኒ ሠናይ ወጾር የኒ ቀሊል» ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀላል ነውና ይላል። «አሐስስ ዘተገድፈ ወእመይጥ ዘኀየ» በውዋዊ የጠፋውን በሚጠት እመልሳለሁ (እሻዋለሁ) በስደት የሄደውን በዓዋጅ እመልሳለሁ ዕዝ.፩፥፩። «እሔድስ ዘተሰብረ ወአጸንዕ ዘደከመ» በኃጢአት የተሰበረውን በንስሐ አድሳለሁ በጣዖት የደከመውን በሃይማኖት አጸናዋለሁ በማለት መልካም እረኝነቱን ያስረዳል። እነሱ ግን «ወይሰትዩ ጽሩየ ማየ» ግብሩን አሥራቱን ይቀበላሉ ወገኖቹ ግን ከሠራዊታቸው የተረፈውን ይመገባሉ፤ ከእህሉም፤ ከዘይቱም፤ ጥሩ ጥሩውን ወስደው አዳፋውን አተላውን ይተውላቸዋልና በእንቢታቸው በደንደሳቸው ይጋፋሉ ደሃውን፤ ደካማውን በሥልጣናቸው ያጠቃሉ በስደት በውዋዊ እስኪበተኑ፤ ለአሕዛብ ምግብ እስኪሆኑ ድረስ ህዝቡን ያጠፉቸዋል፤ እርሱ ግን ወገኖቹን ከመኳንንቱ ከነገሥታቱ አድኖ ዳግም ለምርኮ ለዘረፋ አይዳርጋቸውም መልካም እረኛነቱን በዚህ ያረጋግጣል። እንዲሁም በዮሐ.፳፩፥፲፯ ቅዱስ ጴጥሮስን ያገለግሉቱን የፍቅሩ መግለጫ ያደረገው በየደረጃቸው መጠበቅ ያለባቸውን ምእመናን በጎቼን ጠብቅ፤ ግልገሎቼን ጠብቅ፤ ጠቦቶቼን ጠብቅ ሲል አስገንዝቧል።

መልካም እረኛ የደከሙትን በጎች በማጽናናት የታመሙትን በማዳከም፤ ግልገሎቹን በመታቀፍ ለበጎቹ ያለውን ፍቅር ይገልጻል።

የመልካም እረኛ መጀመሪያ ለበጎቹ የሚጨነቅ፤ የሚያስብ በመሆኑ ወደ ለመለመ መስክ ወደ ጠራ ውሃ ያሰማራቸዋል፤ ከሌባ ከተኩላ ይጠብቃቸዋል። ፊት ለፊትም ይሄድላቸዋል። እነሱም እሱን አብነት አድርገው ይከተሉታል። በጎቹንም ያውቃል በጎቹም ያውቁታል። የማያውቁትን [illegible] የከተሉትም። መልካም እረኛ በጎቹ እንዳይጠሙ፤ እንዳይራቡ፤ እንዲጨነቅ መልካም እረኛ ክርስቶስም ምእመናኑን ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ፤ በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ያመኑበት፤ ሊቀበሉት ስለአላቸው መንፈስ ቅዱስ ተናግሯል። ዮሐ.፯፥፴፯–፴። ይህንን የሕይወት ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ለዘላለም አይጠማም። እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የሕይወት ምንጭ ነውና። ዮሐ.፬፥፲፫–፲፬። የዚህ ዓለም እረኛ ምንም ለጊዜው የጠራ ውኃ ቢመርጥ ቆይቶ የሚጐሽ የሚደፈርስ ጥራጊ ቆሻሻ የሚወድቅበት የሚደርቅ እና ዳግም የሚያስጠማ ነውና የሕይወት ውኃ ሊሆን አይችልም። ይህን የሕይወት ውኃ ከባሕርዩ የሚፈልቅ ደግሞ የማያስጠማ የሰጠን መልካም እረኛ ነው።

የዚህ ዓለም እረኛ በጎቹን ለጊዜው ወደ ለመለመ መስክ ቢያሰማራቸው፤ ቆይቶ የሚደርቅ በጭቃ እግር የሚረገጥ ደግሞም የሚያስርብ ልምላሜውም ወቅትና ጊዜ የሚጠብቅ ነው። መልካሙ እረኛ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰጠው ምግብና መጠጥ ግን «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁል ጊዜ ከቶ አይጠማም» ይላል። ዮሐ.፮፥፴፭–፴፮። የዚህ ዓለም እረኛ ስለበጎቹ ሕይወቱን አሳልፎ አይሰጥም መልካሙ እረኛ ክርስቶስ ግን ስለ በጎቹ ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ ከበጎቹም በፊት ተላልፎ የሚሰጥ ነው። ምክንያቱም ዓለም የምትድነው በእኔ ደም ነው ብሏልና ይህም ምን ያህል ሰውን መውደዱን ያስረዳል። ከዚህ በፊት የሕዝብ እረኛ የነበሩ ሙሴ ዳዊት ስለ ሕዝባቸው ሲሉ [illegible] ቆርጠው እንደ ተነሱ በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ እንረዳለን። ሙሴ ሕገ ኦሪትን በደብረ ሲና ከእግዚአብሔር ለመቀበል ሄዶ ሳለ ቢዘገይ፤ እስራኤል፤ «አሮን አሮን ግብር ለነ አማልክተ ለየሐውሩ ቅድሜነ ወይጸብኡ ጸረነ» አሮን፤ በፊት በፊታችን የሚሄዱ ጠላቶቻችንን ድል የሚነሱ (የሚቃወሙ) አማልክት ሥራልን አሉት። እስመ ዝኩስ ሙሴ ዘአውጽአነ ምድረ ግብጽ ኢነአምር ከመ ምንተ ኮነ፤ ይህ ከግብጽ ያወጣን ሙሴ፤ አመሌ አመሌ ሲል ያየት የደብረ ሲና እሳት በልታው እንደሆነ ወይም ወደ ግብጽ ሲሄድ ኤርትራ አሰጥሞት እንደሆነ አለበለዚያም ወደ አማቱ አገር ወደ ምድያም ሲሄድ አውሬ በልቶት እንደሆነ አናውቅም ብለው አሮንን ባስገደዱት ጊዜ አሮን

www.ethiopianorthodox.org

ስለ ፈራቸው ጣዖት አቁም እስራኤል ሆይ ከግብጽ ያወጡህ አማልክት እኒሕውልህ አለ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ተቆጣ በእስራኤልም ላይ መዓት እንደሚያመጣ ሙሴንም ከእነርሱ ለሚበልጥ ህዝብ እንደ ሚሾመው ቢጠይቀው እነርሱን ከምታ ጠፋቸው ከመዘገብከኝ የሕይወት መጽሐፍ እኔን ፋቀኝ ብሎ ሕይወቱን ለሚጠብቃቸው አሳልፎ ለመስጠት ወሰነ። ዘጸ.፴፪። ዳዊትም መልአክ መደምሰስ በዓውደ ኦርና የሚጠብቃቸውን ሕዝቦች ባጠፋ ጊዜ ምንተ ገብሩ አሉ አባግዕ እንዘ እነኖላዊሆሙ ዘአበሰኩ እኒህ በጎች ምን ሠሩ፣ እኔ ጠባቂያቸው እረኛ ቸው በድዬ ሳለ ስለዚህ የታዘዘው መቅሰፍት በእኔና በቤተሰቦቼ ይሁን አለ። ስለ ወገኖቹ ፍቅርም የራሱንና የቤተሰቦቹን ሕይወት አሳልፎ ለመስጠት ወሰነ። መልካም እረኛ ይሏል ይህ ነው። ፪ሳሙ.፳፬። እረኞች የሚላቸው በብሉይ ኪዳን እግዚ አብሔር የመረጣቸው መሳፍንቱ መኳንንቱ ነገሥታቱ ካህናቱ ናቸው።

በሐዲስ ኪዳንም እስመ ኢይሰየም መኮንን ዘእንበለ እም ኀበ እግዚአብሔር ይላልና ያለ እግዚአ ብሔር ፈቃድ መሾም መመረጥ ስለማይቻል ሁል ጊዜ መሪዎች ከእግ ዚአብሔር ይላካሉ። እግዚአብሔር፣ የላከውም መምህር የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራል። ዮሐ.፫፥፴፬። ነገር ግን እግዚአብሔር ያልላካቸው በእግ ዚአብሔር ስም የሚነግዱ እግዚ አብሔር ያላዘዘውን በስሙ በድፍረት የሚናገሩ ወይም በሌሎች አማልክት ስም የሚናገር ነቢይ እርሱ ይገደል። እግዚአብሔርም ያልተናገረውን ቃል እንደ ተናገረ የምናውቀው ያ የተናገ ረው ቃል ሳይደርስ ሲቀር ነው። ዘዳ.፲፰፥፲፭–፳፪።

ስለዚህም ዛሬ ከእግዚአብሔር ተልከናል እያሉ ከነቢያት፣ ከሐዋ ርያት፣ ከሊቃውንት በተላ ለፈው ትምህርተ ሃይማኖት ፀንታ የኖረ ችውን የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት ለማናጋት የመጡትን የዘመኑ ሐሳውያን መሲሕ መጋለጥ ይኖር ባቸዋል። መልካመ እረኛ ከእግዚ አብሔር የተላከ መሆኑን የምናረ ጋግጥባት፤

፩. የተናገረው ቃል የሚደርስ በመሆኑ ነው።

፪ኛ. የተናገረውን በተግባር የሚፈጽም መሆኑን ነው። ምክንያቱም የተናገረውን በተግባር የማይፈጽም ከሆነ አስመሳይና አታላይ ነው እንጂ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ሊሆን አይችልም። መጽሐፍ ለሌላው የምታስተምረውን ራስህን እንዴት አታስተምርር? ተው የፋና የገንዳ ይደርስብህ የለምን? ፋና ለሌላ ሲያበራ እሱ ይከስላል። ገንዳም ሌላውን ሲያጠራ እሱ ያድፋል። ሌላውን ሲያለመልም እርሱ ይደርቃልና ሮሜ.፪፥፳፩። ምሳሌ፤ አንድ ሊቅ ትርጓሜ መጻሕፍት እያስተማሩ ሳለ አንድ የራበው፣ ጐን የራቀው ሰው መጥቶ ስመ እግዚአብሔር ጠርቶ ራበኝ ጠማኝ ሲላቸው ረሀብስ ኢሰሚአ ቃለ እግዚአብሔር፤ ረሀብ ማለት የእግዚአብሔርን ቃል አለመስማት ነው ተቀመጥ አድምጥ አሉት። እርሱም ርቦታልና ጥሎአቸው በአቅራቢያቸው ወደምትገኝ ሴት ሲሄድ ጥሬ እያነፈሰች አገኛትና ስመ እግዚአብሔር ጠርቶ ለመናት፤ እርሷም ከያዘችው ጥሬ ቆንጥራ ብትሰጠው ነፍሱ ገብታ ሰውነቱ ተመለሰ። እዩት በዚህ ጊዜ እኒያ መተርጐም ንሕነ ናነብብ ወይእቲ ትተረጐም። ዛሬ በዘመናችን ተርጓሚ፣ ሰባኪ፣ አስተማሪ አለ። ግን የተናገረውን እሱ የማይፈጽመው ከሆነ አንባቢ እንጂ ተርጓሚ አይደለም። እንዲሁም አንድ አስተማሪ በማቴ.፲፪፥፵፮ ላይ ከደቀመዛሙርቱ እንዱ...መጥቶ እነሆ ወንድሞችህና እናትህ ሊገናኙህ መጥተው ከደጅ ቆመዋል አለው። ለነገረው ሰው እንዲህ አለው፣ እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው? አለና እጁን ወደ ደቀመዛ ሙርቱ አመለከተ፤ እናቴም ወንድ ሞቼም እነሆ በጉባዔ ያሉ ሕዝብ ናቸው አላቸው። የሰማይ አባቴን ፈቃድ የሚፈጽም ሁሉ እናቴም ወንድሜም እሱ ነው። አለና በዚህ ጉባኤ ያለነው ሁሉ እህትማማቾች ወንድማማቾች ነን ብሎ አስተምሮ ወደ ቤቱ ሄደ። ከቤቱ ከሄደ በኋላ ለዘበኛው ማንም ሰው እኔን ቢጠይቅህ የሉም በል ብሎ ትእዛዝ ሰጠው። በዚህ ጊዜ ትምህርቱን በጉባኤ ሲከታተል የነበረው አንድ ሰው የአስተማሪውን ቤት ጠይቆ ሄደና ባገኘው ጊዜ በር ቆረቆረ። በረኛውም ምነው ቢለው ወንድሜን ላነጋግር እፈልጋለሁ አለ። እሱም እንደ ታዘዘው የሉም አለው። ጭቅጭቅ በተነሣ ጊዜ ያ አስተማሪ ወጣና ምንድነህ? አለው። ያሰው እኔ እኮ ወንድምህ ነኝ አነጋግረኝ አለው። ያ አስተማሪ ፈረንጅ ነበርና ይህኛው ጠያቂው አፍሪቃዊ ስለሆነ እንኳን እንዳንተ ያለ እንደኔ ያለ ወንድምም የለኝ አለው። እዚያኮ ሲያስተምሩ በትምህርት ገበታ ያለነው ወንድ ማማቾች ነን ስላሉ ትምህርቱን በጉባዔ ከተከታተሉት አንዱ እኔ ነኝና ወንድምህ ነኝ አለው። አስተማሪውም መልሶ ያማ ከዚያው ነው እንጂ ከዚህ አይደለም አለ።

ስለዚህ ይህ አስትማሪ የተናገ ረውን በተግባር የማይፈጽም በመን ፈሳዊ ሕይወት የባህርይ ለውጥ የማይ ታይበት አታላይና አስመሳይ ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህ የተናገሩትን በተግባር አለመፈጸም፣ በእግዚአ ብሔር ስም ሌላውን እያስተማሩ

www.ethiopianorthodox.org

የራስን ሕይወት ካላስተማሩበት እግዚአብሔርን ማስደብ ይሆናል።

እውነተኛው መልካም እረኛ ግን እስመ ስምዐ ቃላቲሁ ምግባሩ ውእቱ እንዳለ መጽሐፍ ነገሩን በሥራው ለመግለጥ፤

፩ኛ. አነ ውእቱ ኅብስተ ሕይወት ዘወረደ እምሰማይ። ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ። ከዚህ ኅብስት የበላም ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ ይኖራል። እኔ የምሰጠው ይህ ኅብስት ሥጋዬ ነው። የዘለዓለም ሕይወት ሊሆን። ስለዚህ ራሱን በኅብስተ ሕይወት መስሎ ሥጋውን በኅብስት እንደሰጠን ያስረዳል። ዮሐ.፮፥፲፩።

፪ኛ. አነ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ባለው መሠረት ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው በደረቅ ግንባር ዐይን ፈጥሮ ብርሃን ሆኖታል።

፫ኛ. አነ ውእቱ ትንሣኤ ወሕይወት ዘየአምን ብየ እመኒ ሞተ የሐየ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ ያመነብኝም ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ባለው መሠረት የአራት ቀን እሬሳ አልዓዛርን ትንሣኤና ሕይወት ሆኖ አስነስቶታል።

፬ኛ. አነ ውእቱ ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት። የሕይወትና የጽድቅ መንገድ እኔ ነኝ፤ ያለ እኔ ወደአብ የሚመጣ የለም። እኔን ተወላዲ ካላለ አብን ወላዲ የሚለው የለም። ዮሐ.፲፬፥፮። ስለዚህም ራሱን በሕይወትና በጽድቅ መንገድ መስሎ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ እንካሳ ሆኖ ለተወለደው ሰው ቅዱስ ጴጥሮስ ብርና ሣንቲም የለኝም በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ ባለው ጊዜ እግሩና ቁርጭምጭሚቱ ፀና ስለዚህ የጽድቅና የሕይወት መንገድ እኔ ነኝ እንዳለው ከእናቱ ማኅፀን ሽባ ሆኖ ለተወለደው ሰው የጽድቅና የሕይወት መንገድ ሆነው። ግብ ሐ.፫፥፩–፲።

፭ኛ. አነ ውእቱ ሐረገወይን ዘጽድቅ ወአቡየ ተካሊሁ ብሎ በተናገረው መሠረት እራሱ በወይን ሐረግ መስሎ ደሙን በወይን ሰጥቶናል። ራሱንም በሕጠተ ሰርናይ መስሎ ሥጋውን በስንዴ ሰጥቶናል። ዮሐ.፲፭።

፮ኛ. አነ ውእቱ አንቀጸ አባግዕ ዘበአማን እውነተኛ በር እኔ ነኝ በእኔ በኩል የገባ ማለት በእኔ ያመነ ሰው ከክሕደት ይድናል፤ ወደ ሃይማኖት ይገባል። ሥራ ለመሥራት ይወጣል። መሠማርያም ያገኛል። ማለት እሳቱን፣ ሥለቱን፣ መስቀሉን ያገኛል ወይንም እኔን አብነት ያደረገ ከፍዳ ወንጌልን ወይወጽእ ለማስተማር ጉባዔን ያገኛል። እንግዲህ ራሱን በመግቢያና በመውጫ መሠማርያ መስሎ የምዕመናን አዳኝ አሠሪ፤ አሠማሪ መሆኑን ያሳያል።

፯ኛ. አነ ውእቱ ኖላዊ ኄር ኢሳ.፵፥፲፩፣ ሕዝ.፴፬፥፳፫ ከዚህም ቸር ጠባቂ እኔ ነኝ። የበጎች ባለቤት የሆነ ለበጎቹ ነፍሱን አሳልፎ እንዲሰጥ፤ እርሱም ለምእመናን ቤዛ ራሱን ለሞት ለሕማም አሳልፎ ሰጥቷል።

ስለዚህ ማንኛውም የመልካም እረኛ ተከታይ የሆነ መንፈሳዊ አስተማሪ ያስተማረውን በተግባር መተርጐም አለበት። ምክንያቱም ተምርጦ መሾም ለማስተማር ነውና «የሹም ሰነፍ ባይለፈልፍ» እንዲሉ። ይህንም ላስተዋለው ለመረመረው ሰው ሹመትን ሺሕ ሞት አስመስሎ ያሳየዋል። መንፈሳዊ ሹመት መሾም እንደ ክርስቶስ መከራ ለመቀበል ምእመናንን ለማገልገል በሥራው ሁሉ ነቢያትን፣ ሐዋርያትን ለመምሰል ነውና።

እውቁ ባለቅኔ መልአከ ብርሃን የመልካሙን እረኛ ሕይወት በቅኔአዊ ምሥጢራቸው ገልጸውታል። ቅኔውም የሚከተለው ነው።

መወድስ ቅኔ፤

እምአፈ አርዌ በግዐ ለእመ አቀበ፤ ኖላዌ አባግዕ አዕላፍ ምንት ኄርውናሁ።

ወምንት ውእቱ ለዘይትአቀብ ረባሁ።

እምአፈ አርዌ በግዐ ድኅረ አቀበ ውእቱ እስመ ይበልዖ ለአርዌ ከማሁ።

ወለእመዝንቱ አይበልዖ እስመ ይሰይጦ በወርቅ ለዘይበልዕ ኪያሁ።

ትርጓሜ

የአዕላፍ በጎች እረኛ በጉን ከአውሬ አፍ ቢጠብቅ ደግነቱ ቸርነቱ ምንድን ነው? ለሚጠብቀውስ በግ ጥቅሙ ምንድን ነው? በጐቹን ከአውሬ አፍ ከጠበቀ በኋላ እንደ አውሬ እሱ ይበላዋልና። እሱ ባይበላውም በጉን ለሚበላ ሰው በወርቅ ይሸጠዋልና ጥቅሙ ምንድን ነው?

ለዓለም

ረባሕሰ ወበቍዔት ለኖላዊነ ትጋሁ

በበትረ መስቀሉ ድኅሪ አቀበ አምአፈ አርዌ አባግዒሁ።

አምጣነ ደሞ ያስቲ እንዘ ያበልዕ ሥጋሁ።

ወኢያወጽኦ መንገለ አፍአ ለዘመጽአ መንገሌሁ።

ትርጓሜ

የመልካሙ እረኛ ትጋትና አጠባበቅ ግን ጥቅም አለው። በመስቀሉ በትር በጐቹን ከተጠበቀ በኋላ ሥጋውን እያበላ ደሙን ያጠጣልና። ወደሱ የመጣውንም ወደ ውጭ አያወጣውምና ሲሉ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለሰዎች ያደረገውን ቸርነት፣ ደግነት ሁሉ ገልጿል። ✣



2nd year, Number2, Meskerem 1992